# መተው

አንጡራ ንብረቱን
 የሚመፀወተው
ቀን የጣለው ጌታ
ጥቃት ያቃተተው፤
በሬውን ቀናይባስ
ላሙን አላት መተው።

# የአዳም ልጅ

ያ’ዳም ልጅነቴ
አሳስቶት ኑሮዬን
የሰው ሥጋ አስበላኝ
ያውም የጌታዬን።

# ጉልቻ

ያ’ርባ ቀን ዕድሉ
ዕጣ ፈንታው ደደር፤
ያልሠራለት ወደር
የዘላለም አቻ፤
ሲቃጠል የሚኖር
ድንጊያ ነው ጉልቻ።

# ድልና መስዋዕትነት

ያለ መስዋዕትነት
ድል የለም ብለውናል
እኛም ድል ለማግኘት
ተማግደን አልቀናል
ግን ስንሰዋለት ለምን ይርቀናል?

# ሀሜታ

የሁላችን አምላክ
በፍቅር ይቅርታው
በመለኮት አፍታው
ብዙ አይሁድ ፈወሰ
ኢየሩሳሌምን ሲያያት አለቀሰ።

አብርሃምን ባረከው፤ ዳዊትን አነገሰው
በግብፅ በርሃ ሙሴንም ቀደሰው
 ወደኛ ሲዞር ግን፤
በምህረት ደብዳቤው
እግዜርን አማሁት
ሲያደላ ታዝቤው።

የካቲት 2007

አብርሃም በየነ